# "የቅንጅት የቀጠናው ተጠሪ የነበሩት አቶ ማተቤ መለሠ ተሰማ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ጋር ተቀላቀሉ"

## ከአቶ ማተቤ መለሠ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

## ክፍል 1

ከምርጫ 97 ወዲህ ወያኔ በኢትዮጵያ ኅዝብ ላይ እጅግ የሠፋና የከፋ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ረገጣ አጠናክሮ ቀጥሎበታል። ዜጎች ያለፍርድ ይገደላሉ፣ ያለፍትህ ይታሰራሉ፣ ንብረታቸው ይዘረፋል፣ መብታቸው ይገፈፋል፣ ይደበደባሉ ከዚህ የተረፉ ቢኖሩ እግሬ አውጭኝ በማለት ወደተለያዩ አቅጣጫዎች መትመሙን ተያይዘውታል።

ይህ የግፍ አዝመራ ከተወቃባቸው መካከል የቅንጅት አባልና የቀበሮ ሜዳ እርሻ ልማት ባለቤትና ዋና ስራ አስካያጅ የሆኑት አቶ ማተቤ መለሠ ተሰማ የሚገኙበት ሲሆን ተጠቃሹ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን በጀቢጠህናን ወረዳ ውስጥ ከ33 ሚልዮን የኢትዮጵያ ብር በላይ በሆነ ካፒታል ዘመናዊ የግል እርሻ ልማት በማቋቋም ሲንቀሳቀሱ የነበሩና በያኔ በጠላትነት እስከፈረጀበት ጊዜ ድረስ በእራሱ መገናኛዎች ወጣቱ ኢንቨስተር የልማቱ አርበኛ ወ.ዘ.ተ. እያለ ሲያወድሳቸው እንዳልነበረ ሁሉ ለእሱ የጎሳ ፖለቲካ ታዳሚ አልሆንም ሲሉት ንብረታቸውን ዘርፎ በየጊዜው ውሎአቸውን ከኢህአደግ ስራ አስፈጻሚ ፍርድ ቤት፣ አዳራቸው እስር ቤት ከማድረጉም በላይ የህዝብን ድምጽ ሰርቆ ቀድሞም ከቃላት ያልዘለለውን ዲሞክራሲ ጨፍልቆ የሚሰራው ግፍ ስላንገበገባቸው በሐይል ለማስወገድ በመወሰን ፊት ለፊት ገጥሞ በትጥቅ እየተፋለመ ያለው የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባርን ተቀላቅለዋል።

አቶ ማተቤ መለሠ ስለ ኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ እንዲገልጹልን የአቀረብንላቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ ፈቃደኛ ስለሆኑ፤ ቃለ ምልልሱን ከዚህ በታች እንደሚከተለው እናቀርባለን።

**ጥያቄ:** አቶ ማተቤ መለሠ ተሰማ በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነው በመገኘትዎ እናመሰግናለን።

**መልስ:** እስኪ ልተንፍሰው ምናልባት ቢበርድ እሳት በሆዴ ውስጥ ታፍኖ ሲነድድ እንደሚባለው በሆዴ ታምቆ በህሊናዮ ታጭቆ ከሚርመሰመሰው መለኪያ መስፈርት መግለጫ ቃላት ከማይገኝለት ታሪክንም ሕዝብንም እግዚአብሄርንም ከማይፈራው ከማያፍረው ከውልደቱ እስከ እለተ ሞቱ ውሸትን ክህደትንና ማጭበርበርን ልብሱና ጉርሱ ከአደረገው ከወያኔ ቡድን ዘረፈ ብዙና አሰቃቂ ድርጊት ቀንጥሬ ጥቂት በመናገር እንድተነፍስ እድሉን በማግኘቴ ማመስገን የሚገባኝ እኔ ነኝ እና ከልብ አመሰግናለሁ።

**ጥያቄ:** ለውይይታችን መግብያ ከህይወት ታሪክዎ ብንጀምር?

**መልስ:** ደስ ይለኛል ነገር ግን የአንድ ሰው ህይወት ሲነገር በአሁኑ በወያኔ ፈሊጥ ከዚህ ክልል ከዚያ ቢሔረሰብ ተወለድሁ የሚለው የተለመደ ሆኗል እኔ ግን ብሔረሰቡን ሆነ ቤተሰቤን የምኮራባቸው እንጂ የሚያሳፍሩኝ ባይሆኑም እዚያ ውስጥ መግባቱን አልወደውም።

ምክንያቱም በወያኔ የጎሳ ፖለቲካ ነቀርሳ የተበከልኩና የምወዳትን አገሬንና የማከብረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የካድኩ መስሎ ስለሚሰማኝ ነው።

በዚህ ፋንታ ኢትዮጵያን የማፈቅር ኢትዮጵያዊነትን የማከብር ኢትዮጵያዊ ነኝ ብል እራሴን ገልጫለሁ ብዮ አምናለሁ::

በሌላ በኩል እድሜዮ 42 አመት የትምህርት ደረጃ የ12ኛ እና በማኔጅመትና በስነጽሁፍ ሁለት ሰርትፍኬቶች ያሉኝ ሲሆን እድሜዬን ለስራ ከደረሰበት ጀምሮ በደርግ መንግስት በወቅቱ አጠራር በሐገር አስተዳደር ሚኒስትር ስር በሚገኙ በጎጃም በሐረርጌ፣ በወለጋ፣ በሸዋ፣ ክፍለ ሐገራት አስተዳደር ጽ/ቤት እየተዘዋወርኩ የዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ኃላፊነት እየተሰጠኝ ለ10 አመት አገልግያለሁ:: በዚህ ወቅትም በሙያው እጅግ ከበሰሉ ምሁራን ጋር አብሮ የመስራት እድሉ ስለገጠመኝ ሳይንስም ጥበብም ከሆነው ከአስተዳደር ሙያ እውቅያናስ ጨልፌ ሰንቄ አለሁ ብዩ አስባለሁ::

ወያኔ ሐገሪቷን እንደወረረ የመጀመሪያ ስራው ያደረገው ኢትዮጵያውያንን ከስራ ማፈናቀል ስለነበር የዚህ ሰለባ በመሆኔ ከ33 ሚሊዮን ብር በላይ በሚሆን ካፒታል የቀበሮ ሜዳ ዘመናዊ የግል እርሻ ልማትን በማቋቋም የደረቅ ጭነትና የህዝብ ማመላለሻ መኪናዎች ገዝቼ በማሰማራት በአንድ እርዳታ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅነት እየተንቀሳቀስሁ በወያኔ አስገዳጅነት የምወዳትን ሐገሬን የማከብረውን የኢትዮጵያውያን ህዝብና የምሳሳላቸውን ቤተሰቦቼን ትቼ ወደ ስደት እስካቀና ድረስ ሰርቻለሁ::

**ጥያቄ:** የቅንጅት አባልነዎት ወደትጥቅ ትግል ሲገቡ ፓርቲዎ ይደግፈዋል ወይ?

**መልስ:** በጣም ጠቃሚና ጥሩ ጥያቄ ነው መልሱ አይደግፈውም ነው:: ምንም እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞራላዊ ስክና በከዳው ስነምግባር በአልገረዘውና በአልተገራው የጫካ የአነጋገር ዘይቤአቸው ትልቁን አሳንሰው ጠንካራውን አኮስሰው ድርጅቱን የነውጥ ማዕከል ብርቅዬና መተኪያ የማይገኝላቸውን መሪዎቹን የጎዳናኮይ ነውጠኛ እያሉ ቢዘልፉም ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ አላማው በሰላም ለአንድነትና ለዲሞክራሲ መታገል ግቡ ህዝቡ በመረጠው መንግስት እንዲመራ ማድረግ ሲሆን መሪዎቹም የሰላማዊ ትግል ደቀመዛሙርት እንጂ በትጥቅ ትግል ለውጥ ለማምጣት መስራት አይደለም የማያስቡት ናቸው::

እኔ ትናንት የወያኔን መሰሪ ሴራ በሰላማዊ ትግል ለማክሸፍ የቅንጅት አባል ሆኜ ታግያለሁ ዛሬ ደግሞ በትጥቅ ትግል ወያኔን ለማንበርከክ ለኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር አባል ሆኛለሁ አንድ ሰው በአንድ ወቅት ለሁለት ድርጅት አባል መሆን ስለማይችል ምርጫዬን ለማስተካከል መብቴን ተጠቅሜ አለሁ ማለትነው::

የስው ልጅ የሚወደውን ተነጥቆ የሚጠላውን እንዲሸከም ሲገደድ ማሩ እንደሬት ይመረዋል ወተቱ እንደ ከሰል ጠቁሮ ይታየዋል በዚህ ግዜ እንቢ ይላል ድሩን ቤቱ የዱር አራዊቱን ጎረቤቱ ያደርጋል ህግን እርሙ አመድን ወንድሙ አድርጎ ይፈረጃል::

በግ ከበረረ የሰው ልጅ ካመረረ እንደሚባለው ይህንን ዘራፊና ገፋፊ የወያኔ ብዱን በመፋለም ቆሞ ሲሞቱ ከመኖር ሞትን በሞት ሽሮ ማለፍን በጸጋ እንድቀበል ያዘዙኝ ማንንም ሳይሆን የእራሴ የህሊና እና የመንፈስ ጉልበቶች ተጋግዘው ስለሆነ ነው የሰላማዊ ትግሉ የገባሁት ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ነው ከቅንጅት ጋር ግኑኝነት የለኝም የምለው::

## ክፍል 2

**ጥያቄ:** ከሐገርዎ ለመውጣት ምክንያት የሆነውን አበየት ነጥብ ቢገልጹልን?

**መልስ:** ሁሉም እንደሚያውቀው ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ምሪት ተዘርቶ ስቃይ የሚበቅልበት ሞት የሚመርትበት የሰዎች በህይወት የመኖር በነጻነት የመኖር የአካል

ነጻነት የማግኘት መብት ተገፍፎ አንድ የአጋዚ ወይንም የፌዴራል ፖሊስ ወታደር ወይም የኢሃደግ ካድሬ በፈለገ ጊዜ በመንገድ ላይ ሲሄድ የሚያገኘውን ሰው ገድሎ ሆስፒታል በማስረከብ የሟች ቤተሰቦች ወደሆስፒታል ሲሄዱ አስከሬን ለመውሰድ ለገዳዩ አንድ ሺ ብር እንዲከፍሉ የሚገደዱበት በአጠቃላይ የህዝብ ሰባዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተገፍፈው የመኖር ዋስትና የከሰመበትና ሁሉም ሞትን በጸጋ ለመቀበል ተዘጋጅቶ በመጠባበቅ ላይ ያለ ከመሆኑም በላይ በግሌም

1ኛ ከ40,000,000 ብር በላይ የሚገመት ንብረቴን ወያኔ የዘረፈኝ በመሆኑ
2ኛ ምክናያቶች እየተፈጠሩ የሃሰት ሰነዶች እየተዘጋጁ በየጊዜው መዋያየ ፍትህ ከማይሰጠው የወያኔ ፍርድ ቤት አዳሬ ወህኒ ቤት በመሆኑ
3ኛ በሃገሬ ላይ ሰርቼ እንዳልበላ ከህብረተሰቡ ጋር እንዳልገናኝ በጥብቅ እየተጠበኩና በህይወት ለመኖር ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ስለወደቀ አካሌን ነጻ ለማውጣትና በህይወት ለመኖር ስል ከወያኔው እስር ቤት አምልጬ ተሰድጃለሁ::

**ጥያቄ:** ከጥቅሉ በኢትዮጵያ የሰባዊ መብት ጥሠት እንዳለ ይነገራል እርስዎም አስቀምጠውታል ምርጫውን ተከትሎ ከተፈጸሙት ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች ጠቅሰው ሊገልጹልን ይችላሉ?

**መልስ:** ግፈኛው የወያኔ ቡድን ምርጫ 97 ተከትሎ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈጸመው የማጭበርበር፣ የማስመሰልና የጭካኔ ስራዎችን ዘርዝሮ ለመጨረስ ማሰብ ዕውቅያኖስን በሻይ ማንኪያ ቆንጥሮ እጨርሳለሁ ብሎ እንደመሞከር ከመሆኑም በላይ ሁሉም ሰው በአንክሮ ተከታትሎታል ብዬ ስለማስብ የሚያውቀውን በመድገም ጊዜ እንዳላጠፋ በመስጋቴ አልገባበትም::

ነገር ግን በተገቢው ሁኔታ አለተገለጹም የምላቸውን እውነንተኛዎች ለመጥቀስ ታክል ከምርጫው በፊት የነበረውን የተቃዋሚ ፓርቲ አበበቅን እስራት ድብደባ ወከባ አፍም ድራሻቸውን ማጥፋት ገድሎ መጣልን ማለት ከተገደሉት ለመጥቀስ እነ ምናሉ መንገሻ፣ አሳየ ታምራት፣ ዘሪሁን አባይ በጠራራ ጸሃይ በፖሊስ ተመትተው የወደቁ ታፍነው ድራሻቸው ከጠፉት እነ ሽመልስ አረጋ፣ ሽረው መኮንን፣ በላቸው ውብቱ የመሳሰሉትን ትተን ከምርጫ ወዲህ

1ኛ በውጭ መገናኛ ብዙሐን ተደጋግሞ የሚነገረው 80 ሰው ሞቷል 40ሺ ሰው ታስሯል የሚል ነው:: ይህ አባባል ያሳዝነኛል:: ሰው የሚበላው አዲስ አበባ ከተማ ለዚያውም መንገድ ዳር የወደቀውን ብቻ ካልሆነ በቀር በየክፍለ ሐገሩና ገጠሩ ያለቀው በትክክል ቢቆጠር በሺዎች የሚቆጠር ህዝብ ነው ያለቀው:: ሌላው የታሰረው ደዴሳ ብቻ 43ሺ፤ ብሪሽለቆ 34ሺ፤ ዝዋይ 12ሺ፤ ሸዋ አሮቢት 8ሺ ህዝብ ነው:: የታጎረው አዲስ አበባ ቃሊቲና ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ እና በየክልሉ ያለውን የተጨናነቀ እስር ቤት ሳንጨምር እንኳን 94ሺ ህዝብ ነው እስር ቤት ያለው::

2ኛ ደብተር ይዘው ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ የ7 አመትና የ11 አመት ህጻናትን ሰው ብለው አጋዚና ፌደራል ፖሊስ ገድሎ የህጻናት ወንድማማቹን አስከሬን ሆስፒታል በማስገባት ታላቅ ወንድማቸው ሔዶ አስክሬናቸው ይሰጠኝ በማለት ሲጠይቅ ሁለት ሺ ብር ክፈል ይባላል:: ለምን ሲል በአነሳው ጥያቄ እሱም ተገድሎ እናት 3ሺ ብር ከፍላ 3 ልጆቿን ቀብራ ልብሷን ቀድዳ ከቤት እንደወጣች ቀርታለች::

3ኛ ለጸሎት ወደ እምነት ቦታ የሚጓዙ የ80 አመት አሮጊትና የ90 አመት አዛውንት በጥይት ተገድለዋል::

4ኛ በጆርባዋ 3 አመት ህጻን ያዘለች እርጉዝ ሴት ከእነ ልጆቿ ተገድላለች::

5ኛ ጎንደር 3 ወጣቶችን ከሚጫወቱበት ወስዶ እመሬት ላይ እንዲተኙ በማድረግ ተረሽነዋል::

6ኛ አዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ነዋሪ የነበሩትን የ10 ልጆች እናት ወይዘሮ ከበቡሽ መልጌን በአሰቃቂ ሁኔታ በጥይት ደብድበው ገድለዋቸዋል፡፡

እነዚህን ለአብነት ጠቀስሁ እንጂ ያለማጋነን በዚህ አይነት ሁኔታ ያለቁት በሺዎች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ በተለይም ተመልካችና ታዛቢ የሌለው በገጠሪቷ ኢትዮጵያ የሚኖረው ወገኖችን ከመቶ አምሳው ለወያኔ አረመኔአዊ ድርጊት ሰለባ ሆኖል አርሶ አደሩ የወያኔ ያደረ ካልሆነ የቅንጅት አባል ወይም ደጋፊ ነህ እየተባለ ይገደላል፣ ይታሰራል፣ ንብረቱ ይወረሳል ከሞት የተረፈውም

1. እንደ እንስሳ የዘር ብልቱን አኮለሽተው ይለቁታል
2. እጁን ወይንም እግሩን ሰብረው አካለ ጎደሉ ያደርጉታል
3. ሚስቱና ልጃገረድ ልጆቹ በወያኔ ሰራዊት ወይንም ካድሬ ይደፈራሉ
4. ቢሞት ቀባሪ ቢታመም ጠያቂ እቤቱ ከደረሰ ደራሹ ይታሰራል
5. ስቃዩን ፈርቶ ባል ከሸሸ ሚስት በእሱ ገመድ ገብታ ፍዳዋን ታያለች

በዚህ አይነት ኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ከከተማ እስከገጠር መቼ ምን እንዴት ይመጣብኝ ይሆን በማለት ስጋው በስጋት እያለቀ ነው፡፡

**ጥያቄ:** ይህንን ግፈኛ ስርአት በሰላማዊ ትግል ለመጣል ታግለዋል አሁን ግን ወደ ትጥቅ ትግሉ የገቡት በኢትዮጵያ ከእንግዴህ ሰላማዊ ትግሉ ፍሬ የለውም የሚል እምነት አድሮብዎት ይሆን?

**መልስ:** አዎ በቅርጹም ሆነ በይዘቱ ከወያኔ መሰሪ ሸር የጸዳ በእውነት ስለሐቅ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት ለህዝቧ ሰላምና ዲሞክራሲ የጠራና የነጠረ አቋም ያላቸውን እውነተኛ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች የሚመሩት ቅንጅት ለአንድነት ለዲሞክራሲ ብቻ ነበር፡፡ ይህ የህዝብ አለኝታና መከታ ፓርቲ መሪዎች ታስረው አባላትና ደጋፊዎቹ ተገድለው ተሰድደው ጽ/ቤቶቹ ተዘግተው የህዝብ ተስፋ መክኖል፡፡ ከዚህ በኋላ በሰላማዊ መንገድ አታግሎ ህዝቡን ለድል የሚያበቃው የትኛው ፓርቲ ይሆናል በዬ ልጠብቅ ታሪካቸውን ለጥቅማቸው ሰብናቸውን ለሆዳቸው የሸጡት እነልደቱ ወይንም በእንደ አያሌው የሚመሩት ኤዴፓ ወይንስ ሲወጠር እያላሉ ሲከር እያራቡ ለፓርላማ ወንበር ብቻ ከሚጣጣሩት ወይንም እንደነ አየለ ጫቢስና ተመስገን ዘውዴ ተለጣፊ ቅንጅትን ለመፍጠር ከሚጣጣሩት ሆድ አደሮችና ከሐዲዎች፡፡ ስለዚህ በእኔ እምነት ወያኔን ጠራርጎ ለማስወጣትና ህዝብን ለነጻነቱና ለዲሞክራሲያዊ መብቱ ለማብቃት ብቸኛው መንገድ የትጥቅ ትግል መሆኑን ስለተገነዘብኩ ነው ትግሉን የተቀላቀልኩት፡፡

**ቃለ መጠይቅ ይቀጥላል**

**16th April 2006**